ethiopia@ethiopianembassy.org

መስከረም 20/2003 ዓ.ም.

ጉዳዩ፡- በኢትዮጵያ ውስጥ አክራሪ የእስላሞች ትንኮሳን በሚመለከት

ለህዝባዊ ሓርነት ትግራይ አምባሲ ጽ/ቤት አባሎችና

ለአምባሳደር ሳሙኤል አሰፋ

ለአቶ ጸሃየ ደባልቀው

ዋሺንግተን ዲሲ

ከጌታቸው ረዳ ሳን-ሆዘ ካሊፎረኒያ አሜሪካ- የኢትዮጵያን ሰማይ ብሎግ አዘጋጅ

www.ethiopiansemay.blogspot.com getachre@aol.com

ይህ ደብዳቤ ስልክላችሁ አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የህወሓት ቡድን ቁም ነገር ይሰራል በሚል ሳይሆን፤ የአንድነት መንግሥት ነው ብላችሁ አምናችሁ የምታገለግሉት ህወሓት አገርን የማስተዳደር ችሎታው እጅግ አሳዛኝና ብቃት የሌለው መሆኑን ታሪክ እንዲመዘግበውና በናንተ ሕሊናም "አንድ ቀን ነብስ ስትዘሩ" የህ የስሞታ ደብዳቤ እንድታስታውሱት ዘንድ በሚል ነው።

እዚህ ግባ የማይባሉ ዩተለያዩ የቆዩ ማሕበረሰባዊ ጥቃቅን ግጭቶች (አንዳንዶቹም ታይተውና ተሰምተው የማያውቁ ችግሮች) ህወሓት ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ቀን ጀምሮ በከፋ መልኩ አድገው ሕብረተሰቡ እርስ በርስ በመጋጨት ብዙ ሺሕ ሰው ህይወት እና ንብረት ለጥቃት ተጋልጧል። በቅርቡ ዛሬ መስከረም20/2003 worthy News (በእኛ ዘመን አቆጣጠር) በፈረንጅ ሰፐተምበር30/2010 በድረገጹ ያወጣው ዘገባ ጅማ ውስጥ ጎዳ በተባለው ጎጥ የመንግሥት ሚሊሺያዎች በክርስትና እምነት ተከታዮች መኖርያ ቤቶች በእሳት ኣጋይተው በረካታ ሳምንታት በቁጥጥራቸው ስር እንዲቆዩ በማድረግ ከታጋቾቹ አንድ ሰው አምልጦ ሁኔታው "ለመንግሥት" መስተዳድሮች አመልከቶ፤ ባመለከተው መሰረት አጥቂዎቹ ሲያመልጡ ከመሪዎቹ አንድ ሰው ብቻ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከዋለ በሗላ በዋስ መለቀቁ http://www.worthynews.com/9539-ethiopian-muslims-burn-down-christian-homes-farms ዘግቦታል። ይህ "ዎርዚ ኒውስ" የተባለ ጋዜጣ ስለ ጥፋቱ ሲያብራራ 25 አክራሪ እስላሞች ተሰባስበው በመዝመት በ85 የክርስትያኖች መኖርያ ቤቶች ላይ እሳት በመለኮስ ያለ መጠለያ እንዲቀሩ

ማድረጋቸውንም በስፋት ዘግቦታል። መንግሥታችሁ ሰላምና መረጋጋት አምጥቻለሁ እያለ ህወሓት ሰራሽ የሆኑ በርካታ ባንዴራዎችን በማውለብለብ በከንቱ ውዳሴ ሲንጎዋለል ስናይ እና ከላይ የተዘገበው በክርስትያንና በአማራው (በመንግሥታችሁ ፤ አነግ እና አክራሪ እስላም ሃይል አባባል “ነፍጠኛ” ) አማኒያን ላይ ለ17 አመታት ሳያባራ እየተደረገ ያለው ተደጋጋሚ ጥቃት ከቶ መቸ ነው ልብ የምትሉት?

ጥቃቱ ስታችሁት አይመስልም! ይልቁንም ካለፉት ዘገባዎች የተለያዩ ዘገባዎች በጥቃቱ ላይ ተካፋይ እየሆኑ ያሉት የመንግሥት ታጣቂዎች እንደሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በናንተ ሚሊሽያ ላይ የሚደርሰው ክስ ተቀበሉት አትቀበሉት ሌላ ክርክር ሆኖ፤- የናንተ መንግሥት ከመለስ ዜናዊ አጉል ፕሮፓጋንዳ (አንዳንዱ ለግጭት መነሾ የሚሆኑ ንግግሮቹን እዚህ ሳንጠቅስ) ማድረግ ሚገባው የምትችሉት ያህል ግን እንዲሰራ አላደረጋችሁም። የአክራሪ እስላሞች ትንኮሳ እየተባባሰ ዓለም አቀፍ እየሆነ መምጣቱ እውን ቢሆንም፡ የናንተ መንግሥት ደምበር ተሻግሮ ከመዳከር ውስጥ ያለው አክራሪ እስላም ጥፋት ሲፈጽም ተከታትሎ ተገቢውን ከመፈጸም ይልቅ ክርስትያኑንም ጭምር አያይዞ ጥፋተኛ በማድረግ ቀውሱ እንዲያገረሽ ያደረገበት ወቅት አለ። “እስልምናው ሲያመቸው በፖለቲካው (ታሪክ/መንግሥት...) እያሳበበ ኢትዮጵያን የሚያውከው ያክራሪ እስልምና ትንኮሳ በጊዜ ሊገታ ካልተቻለ የባሰ ሐዘንና ግጭት ይሆናል። በየጊዜው የሚፈጽሟቸው ትንኮሳዎች እያደጉ ነው። ቁርአን ተቀደደ ፤እስልምና ተናቀ፤ተገፋን በሚሉ ፕሮፓጋንዳዎች የተነሱ የትንኮሳ እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ አድጎ ባሁኑ ጊዜ ለመስማት እና ለማየት የሚዘገንን በሰው ልጅ ያንገት ቆረጣ ግዲያ፤ የቤት ቃጠሎ ፤ካሕናትን ሻሽ በማስወለቅ፤ያንገት ማተብ በመበጠስ (ያውም በጠራራ ፀሐይ አዲስ አበባ ውስጥ!)፤ክርስትያን ሴቶችን በመድፈር፤በገዳማት፤አብያተ ክርስትያናት ፊት ለፊት ለመስጊድ ማሰሪያ ቦታ ካልተሰጠን እስልምና ተንቋል በማለት ለትንኮሳ መነሳሻ ምክንያት መፈለግ፤ ክርስትያን ሥርግ ቤት በመግባት መጽሐፍ ቅዱስን በመቅደድ ዳስ ውስጥ እንደ ቀጤማ ጉዝጓዝ በመነስነስ ብዙ ትንኮሳዎችን ፈጽሟል። በተንኮል ትንኮሳውን ለማባባስ ሆን ብሎ በጥናት የተጠና ውንጀላ ማለትም ቁርዓን የሽንት ቤት መጸዳጃ ሆኗል በማለት ባንድ ዜጋ ላይ የደረሰው ጥቃት እና የረብሻ ማስነሻ ተንኮሉ በመረጃ እንደተጋለጠ ይታወሳል (ያናንተ ዜና ማሰራጫ ግን ያወሩት ቃለ አጋኖ ነበር)።

በዚህ አላቆመም። ሁለት ሦስት በመሆን ሰይፍና ጠመንጃ ይዘው ወደ ቤተክርስትያን በመግባት (በክርስትያን ሕግ “መስቀል” እንጂ ቀሳወስት ሰይፍና ጠመንጃ መያዝ እንደማይፈቀድላቸው አክራሪ እስላሞቹ ያውቃሉ) “አላህ ወአክበር!” በማለት ቤተክርስትያን ውስጥ የተሰቀሉት የእምነት አማልክት ስዕልን ማውረድ ተደጋግሞ ታይቷል። ገዳማት ተቃጥለዋል።ባህታዊያን በሰይፍ አንገታቸው ተቀልቶ ተጥሏል፤ በወሎ/ከሚሴ በሐረር ገለምሶ እና በርካታ አካባቢዎች ክረስትያኖች ወደ ጥምቀት ደመራ

/ወይንም ዓመታዊ በዓል ለማክበር ሲወርዱ ወይንም ግሸን ማርያም ደረሰው ሲመለሱ የተፈጸመው ጥቃትና ለመመዝገብ የሚያደክሙ በርካታ ጥቃቶች በክርስትያን አማኞችና ሕይወት ለ17 ዓመት ህወሓት ከነገሰ ጀምሮ የደረሰ አታውቁትም አልልም። በዚያ ጥቃት ክርስትያኑ ትዕግስት ባያሳይ ጥቃቱ ምን ያህል ርቀት ይኼድ እንደነበር አስተዋይ የሚገምተው ነው። አክራሪው እስላም ከየት ተነስቶ ወድየት እየገሰገሰ እንዳለ ጉዘው ለመረዳት የሚያዳግታችሁ አይመስለኝም።

መንግሥት አጥቂ ክፍል በቁጥጥሩ ሲይዝ ግለሰባዊ ግጭት አስመስሎ የሚፈርጀው ሚዛን ማቆም እንዳለበት ሳሳስብ፤ራሱ መገናኛ (ሚዲያዎችም) ሳያውቁም ሆነ አውቀው የአክራሪው እስላም "መብታችን ተገፈናል"-ፕሮፓጋንዳ ተሸፋፍኖ የሚሰጠው ውሸት ከማራገብ መቆጠብ ይኖርባቸዋል። ተጋንኖ የሚቀርበው የእስለምና ዜግነት መጣስ ወዘተ...መገናኛ አውታሮች በጥሞና መመርመርና በውሸት ወንዝ ከመጉረፍ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። ለመብት መከራከር ተገቢ ሆኖ እያለ ነገር ግን መብት ስላልተፈጸመ ምንም በሌለበት ዜጋ ላይ የግድያ ውንጀል እና ሰላምን የሚነሳ ትንኮሳ መፈጸም በማንኛውም ሕግ ተቀባይነት ስለሌለው የመንግሥት መገናኛ አውታሮች ትክክለኛ የጋዜጠኛ ድርሻቸውን መወጣት ይገባቸዋል። በመንግሥታችሁ ውስጥ በወታደራዊ ስራዎች ጠመንጃ በታጠቁ ክፍሎች፤ በከፍተኛ ሓለፊነት እና በየጽ/ቤቶቹ ተመድበው የሚሰሩ የእስልምና ተከታዮች "የአክራሪ እስላሞች" ትንኮሳ በጽኑ መቃወም እና ከሕዝብ እንዲነጠሉ በትጋት መስራት እና ማውገዝ ከአንድ በጎ የእስልመና ስነ ምግባር ተከታይ የሚጠበቅ ነው።

አክራሪ እስልምና ከራሱ አባላት በቀር ሰው ሁሉ እንደ ሰይጣን እና እንደ ጠላት ስለሚያይ በመንግሥት ሃላፊነት የተቀመጣችሁ ዜጎች ሁሉ የዜና አውታሮቻችሁ ሃቁን እየሸፈኑ አሳዛኝ የሕዝብ ግጭት በውጭ የዜና ዘጋቢዎች ሲዘገብ የእናንተ ድረገጾችና ሚዲያዎች ለምን እንደሚሸሽጉት አሳዝኖኛል።ስደቱ በረከቱ፤ችግሩ ስሞታው ጭሆቱ ግድያው በረከተ! በናንተ ዘመን ምን ያልተደረገ አለ? እንዴት ያን ያህል ጥቃት ያደረሰ በዋስ ይለቀቃል (ያዉም ግጭትን የሚቀሰቅስ ወንጀል!) ስለ ጉዳዩ የምትሉት ነገር ካለ መልሱን በተጠቂዎቹ ስም እጠባበቃለሁ። የዚህ ቅጂ ለሕዝቡ/ሚዲያው ይፋ ይሆናል።

ጌታቸው ረዳ

የኢትዮጵያ ሰማይ የህዋ ሰሌዳ አርታኢ

www.ethiopiansemay.blogspot.com getachre@aol.com 408 561 4836